## Montgomery County Public Schools
## ስንክልና ያላቸው ተማሪዎች ቤተሰቦችን የመደገፍ አገልግሎቶች

The Department of Special Education Services/የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች መምርያ (DSES) በIndividualized Education Program/የልዩ ትምህርት ፕሮግራም የውሳኔ አወሳሰድ ሂደት አማካይነት የተማሪን አገልግሎቶች ፕላን በማድረግ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን፣ ከተማሪዎችና የት/ቤት ሰራተኛ አባሎች ጋር፣ እንድ ዋጋ/value እንዳላቸው ሽርኮች አድርጎ ይመለከታቸዋል። ለልዩ ትምህርት ብቃትንና አገልግሎቶችን በሚመለከት ስለ ሂደቶችና ቅደም-ተከተሎች ግንዛቤ እንዳላቸው ለማረጋገጥ DSES ለወላጆች/አሳዳጊዎች መመርያ ያቀርባል። በተጨማሪም፣ የDSES ሰራተኛ አባሎች ለሁሉም ተማሪዎች የበለጠ የትምህርት እድሎችና ስኬት አወንታዊ የወላጅ-ት/ቤት ሽርክናዎች ለመንከባከብ ያገለግላሉ። የልዩ ትምህርት ክላስተር ተቆጣጣሪዎች እና የፕሮግራም ተቆጣጣሪዎች፣ ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር፣ ለወላጆች/አሳዳጊዎች እንደመገናኛ/ኮንታክት ሆነው ያገለግላሉ። DSES ከልዩ ትምህርት ፕሮግራሞች፣ የሂደት መከላከያዎች፣ እና የተለመዱ ጥያቄዎች ጋር የተያያዙ ኤሌክትሮኒክ መገልገያዎች እና የአመራር ሰነዶች ለወላጆች/አሳዳጊዎች ያቀርባል። የኤሌክትሮኒክ መገልገያዎች በDSES ድርጣቢያዎች በ*www.montgomeryschoolsmd.org/departments/special-education/* ይገኛሉ እናም ከተጠየቀ በህትመትም ይገኛሉ። በMontgomery County ውስጥ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን በሚመለከት ለተጨማሪ መረጃ፣ እባካችሁ DSESን በ301-279-3135፣ 850 Hungerford Drive—Room 230, Rockville, Maryland 20850 ወይም በ301-279-3125 TTY ተገናኙ።

**Child Find Services/ቻይልድ ፋይንድ አገልግሎቶች እና ድጋፍ ለቤተሰቦች፡-**

- **ህፃናትና ትንንሽ ልጆች**
  ከትውልድ እስከ 3 አመት እድሜ ለሆኑ ልጆች ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለ ልጃቸው እድገት ቅሬታዎች ካሏቸው ግምገማ ለመጠየቅ Montgomery County Infants and Toddlers Program/የህፃናትና የትንንሽ ልጆች ፕሮግራምን በ240-777-3997 መገናኘት አለባቸው።

- **ቅድመ-ት/ቤት**
  የChild Find ክፍል ከሶስት አመት እድሜ እስከ ሙአለህፃናት ለሚገኙ ልጆች ነፃ የእድገት ምርመራዎች/ግምገማዎች ይሰጣል። በተጨማሪ አስቀድሞ ስንክልና አለው/አላት ተብሎ/ላ የተለየ/ች የቅድመ-ት/ቤት እድሜ ልጅ ያላቸው ወደ Montgomery County የመጡ አዳዲስ ቤተሰቦች የመጀመርያ መግቢያ ጣቢያቸው ነው። ነዋሪ ያልሆኑ ቤተሰቦች በMontgomery County በሚገኝ ቅድመ-ት/ቤት ወይም የህፃን መንከባከቢያ ማእከል ስለሚ(ምት)ከታተል ልጃቸው የእድገት ቅሬታ ካላቸው Child Find ክፍልን በተጨማሪ መገናኘት ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ የሚከተለውን ተገናኙ፡-

  - የChild Find ሰራተኛ አባል ከ8:30 a.m. እስከ 5:00 p.m.፡- 301-230-5966
  - የስፓኒሽ መስመር፡- 301-230-5967
  - 24-ሰአት Child Find መቀበያ መስመር፡- 301-947-6080
  - Child Find መቀበያ መስመር፡- 301-947-6080

- **የት/ቤት እድሜ**
  የትምህርት እድሜ (K–21) ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች የልዩ ትምህርት ግምገማ አገልግሎቶች በሚመለከት መረጃ ለማግኘት የሰፈራቸውን ት/ቤት መገናኘት አለባቸው።

- **የግል/በጣም የተወሰነ**
  የግል/በጣም የተወሰኑ ተማሪዎች (K–21) ወላጆች/አሳዳጊዎች በ301-279-3166 Division of Business, Fiscal and Information Systemsን መገናኘት አለባቸው።